# ለእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

## ለድንገተኛ እርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

**ለድንገተኛ እርግዝና መከላከያ ክኒን – ያለ መከላከያ ወሲባዊ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ የማርገዝ እድልን ለመቀነስ የሚተቅም ዘዴ ነው።**

| ዘዴ | ለድንገተኛ እርግዝና መከላከያ ክኒን: ulipristal (UPA-EC)<br> | ለድንገተኛ እርግዝና መከላከያ ክኒን: levonorgestrel (LNG-EC)<br> | በማህጸን ውስጥ የሚቀመጥ መሳሪያ (IUD)<br> |
|---|---|---|---|
| **ውጤታማነት** | • 100% ውጤታማ አይደለም<br>• ቀደም ብሎ መውሰዱ በበለጠ ውጤታማ ይሆናል<br>• LNG-EC ጋር ሲነጻጸር የበለጠ ውጤታማ ነው። | • 100% ውጤታማ አይደለም<br>• ቀደም ብሎ መውሰዱ በበለጠ ውጤታማ ይሆናል<br>• LNG-EC ጋር ሲነጻጸር ውጤቱ አነስተኛ ነው። | • ያለመከላከያ ወሲባዊ ግብኙነት እንደተፈጸመ በ5 ቀናት ውስጥ ካስገቡት 99%ውጤታማ ይሆናል። |
| **ይህ ምንድን ነው?** | • አቫሪ እንቁላል እንዳያመርት ይከላከላል ወይም ያዘገያል | • አቫሪ እንቁላል እንዳያመርቱ ይከላከላል ወይም ያዘገያል<br>• እንዲሁም እርግዝናን ለመከላከል የማህጸን አቀማመጥን ሊቀየር ይችላል። | • ትንሽ ፕላስቲክና የኮፐር እርግዝና መከላከያ መሳሪያ<br>• ስፐርም ከእንቁላል ጋር ተገናኝቶ እንዳያፈራ ያግደዋል |
| **ይህን እንዴት ይጠቀማሉ?** | • ያለመከላከያ ወሲባዊ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ ወዲያውኑ መውሰዱ ጥሩ ነው | • ያለመከላከያ ወሲባዊ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ ወዲያውኑ መውሰዱ ጥሩ ነው | • በሀኪም ወይም ልዩ ስልጠና ባገኘ አዋልጅ ነርስ በኩል በማህጸንዎ ውስጥ መሳሪያውን IUD ለማስቀመጥ ቀጠሮ ያስይዙ |

VICTORIA State Government | Health and Human Services

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • ያለመከላከያ ወሲባዊ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ እስከ አምስት ቀናት(120 ሰዓታት) መውሰዱ ይመረጣል<br>• ጡት የሚያጠቡ ወይም አንዳንድ መድሃኒቶች የሚወስዱ ከሆነ ይህ አይመከርም። ስለዚህ ጉዳይ በፋርማሲ ሠራተኛ በኩል ምክር ይቀርብልዎታል። | • ያለመከላከያ ወሲባዊ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ እስከ ሶስት ቀናት (72 ሰዓታት) መውሰዱ ይመረጣል<br>• በሁሉም እድሜ ገደብ ያሉ ሴቶች ይህን መውሰድ ይችላሉ። | • ከዚያም ቢያንስ እስከ አስር ዓመታት ባለበት ቦታ መቀመጥ ይችላል። |
| **ይህን የት ማግኘት ይችላሉ?** | • ያለ ሀኪም ማዘዣ ወረቀት በፋርማሲዎች በኩል ይቀርባል | • ያለ ሀኪም ማዘዣ ወረቀት በፋርማሲዎች ይቀርባል | • የሀኪምና ቀጠሮ ይዘው ከሰለጠነ ጤና ባለሙያ ጋር ያገኙታል |
| **ሌሎች ግምት ውስጥ የሚገቡ***<br><br>* ማሳሰቢያ: በወሲባዊ ግንኙነት ለሚተላለፍ በሽታዎች (STIs) መከላከያ ኮንዶም ብቻ ነው። | • እንደ መደበኛ የርስዎ እርግዝና መከላከያ ዘዴ ተደርጎ መወሰድ የለበትም<br>• ከ LNG-EC በላይ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል | • እንደ መደበኛ የርስዎ እርግዝና መከላከያ ዘዴ ተደርጎ መጠቀም የለበትም | • ለብዙዎች ሴቶች አስተማማኝ ሲሆን ምንም ልጅ ላልወለዱ ወጣት ሴቶችንም ያካትታል። |

በቪክቶሪያ መንግሥት ሥልጣን ያገኘና የታተመ፤ አድራሻ 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria, የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፤ January 2019.
በድረገጽ <http://healthtranslations.vic.gov.au/> ላይ ቀርቧል።